legal aiddc

መብትዎን ይወቁ

# Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ]

## Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] ምንድን ነው?

Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] በ DC ውስጥ ለሚኖሩ፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነገር ግን ለ Medicaid [ሜዲኬይድ] ብቁ ለመሆን ከተቀመጠው ወሰን በላይ ገቢ ለሚያገኙ ሰዎች የጤና መድህን የሚሰጥ አዲስ የጤና መድህን ፕሮግራም ነው። ቀደም ሲል Medicaid [ሜዲኬይድ] የነበራቸው አንዳንዶች የ Medicaid [ሜዲኬይድ] የገቢ ወሰን ዝቅ ማለቱን ተከትሎ ከጃንዋሪ 1 ቀን፣ 2026 ዓ.ም ጀምሮ ወደ Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] ተዛውረዋል።

ፕሮግራሙ የዶክተር እና የሆስፒታል ጉብኝቶችን፣ የተወሰኑ የቤት ውስጥ የጤና እንክብካቤዎችን፣ የታዘዙ መድኃኒቶችን እና ሌሎችንም አገልግሎቶችን ይሸፍናል።

## ለ Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] ብቁ የሚሆነው ማን ነው?

- ዕድሜያቸው 21-64 የሆኑ
- የ US [ዩኤስ] ዜጎች ወይም "በህጋዊ መንገድ የሚኖሩ" (በህጋዊ መንገድ የሚኖሩ ስደተኞች ብቁነት ሁኔታ ሊለወጥ ይችላል)
- ለ Medicaid ብቁ ያልሆኑ
- በአሰሪ ለሚቀርብ "በዋጋ ተመጣጣኝ" የጤና ሽፋን ብቁ ያልሆኑ
- ዝቅተኛ የቤተሰብ ገቢ ያላቸው (ከታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)

## Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] የትኞቹን የገቢ መጠኖች ይሸፍናል?

| **የቤተሰብ ብዛት (አዋቂዎች + ልጆች)** | **ብቁ የሚያደርግ ወርሃዊ የገቢ መጠን (የ US [ዩኤስ] ዜጎች)*** | ብቁ የሚያደርግ ወርሃዊ የገቢ መጠን (በህጋዊ መንገድ የሚኖሩ ስደተኞች)† |
|---|---|---|
| 1 | $1,835 - $2,660 | $0 - $2,660 |
| 2 | $2,489 - $ 3,607 | $0 - $3,607 |
| 3 | $3,142 - $4,553 | $0 - $4,553 |
| 4 | $3,795 - $5,500 | $0 - $5,500 |
| 5 | $4,448 - $6,447 | $0 - $6,447 |
| 6 | $5,101 - $7,393 | $0 - $7,393 |

* በተጨማሪም ህጋዊ የቋሚ ነዋሪነት መብት ያላቸውን፣ የ *COFA [ኮፋ]* ስደተኞችን፣ እና የ *Cuban [ኩባን]* እና የ *Haitian [ሀይቲያን]* ገቢዎችን ያካትታል።
*†* ሽፋኑ የሚወሰነው ለፕሮግራሙ በተመደበው የዲሲ በጀት መሠረት ነው።

## እንግሊዘኛ ቋንቋ በሚገባ መናገር የማልችል ብሆንም ማመልከት እችላለሁ?

አዎ። የዲሲ ህግ የሚለው በእርስዎ ቋንቋ መንግስት ሊያስተናግድዎት እንደሚገባ ነው። ምን ዓይነት ቋንቋ መጠቀም እንደሚችሉ ለኤጀንሲው ያሳውቁ።

# ለ Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

ከሚከተሉት መንገዶች በአንዱ ማመልከት ይችላሉ፦

1. **1. በበይነመረብ (ኦንላይን)፦ በ DCHealthLink.com** አካውንት ይክፈቱ እና የ **DC Health Link** [ዲሲ ሄልዝ ሊንክ] ማመልከቻውን በኦንላይን ይሙሉ
   - *ቀደም ሲል District Direct [ዲስትሪክት ዳይሬክት] የነበረዎት ከሆነ፣ በተመሳሳይ የ District Direct [ዲስትሪክት ዳይሬክት] የተጠቃሚ ስም እና የይለፍ ቃል በ DC Health Link [ዲሲ ሄልዝ ሊንክ] አካውንት ሊኖርዎት ይችላል
2. **በወረቀት፦** የወረቀት ማመልከቻውን በመሙላት በፖስታ የሚከተለው አድራሻ ላይ ይላኩ ለ፦ DC Health Link, Department of Human Services, Case Records Management Unit, P.O. Box 91560, Washington, DC 20090
3. **በ ESA [ኢኤስኤ] አገልግሎት ማእከል፦** በሚያመለክቱበት ሰዓት ደረሰኝ ይጠይቁ። ከእነዚህ ማእከላት አንዱን በአካል በመጎብኘት፦

| **Anacostia Service Center** | **Congress Heights Service Center** | **H Street Service Center** | **Fort Davis Service Center** | **Taylor Street Service Center** |
|---|---|---|---|---|
| 2100 Martin Luther King Jr. Ave. SE<br>(202) 645-4614 | 4001 South Capitol St. SW<br>(202) 645-4546 | 645 H St. NE<br>(202) 698-4350 | 3851 Alabama Ave. SE<br>(202) 645-4500 | 1207 Taylor St. NW<br>(202) 576-8000 |

# ካመለከትኩ በኋላ ምን ይከሰታል?

ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ በፖስታ ወይም በኦንላይን አካውንትዎ በኩል ማስታወቂያ ይደርስዎታል። ከ Managed Care Organization (MCO) [ማኔጅድ ኬር ኦርጋናይዜሽን (ኤምሲኦ)] ጋር በ Managed Care Plan ውስጥ ይመዘገባሉ። ሦስቱ የ MCO [ኤምሲኦ] ፕላኖች AmeriHealth Caritas [አሜሪሄልዝ ካሪታስ]፣ CareFirst BlueCross BlueShield [ኬርፈርስት ብሉክሮስ ብሉሺልድ] እና MedStar Family Choice [ሜድስታር ፋሚሊ ቾይስ] ናቸው። የበለጠ ለማወቅ dchealthlink.com ን ይጎብኙ ወይም ወደ Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] ደንበኞች አገልግሎት በ (855) 532-5465 ይደውሉ።

# የገቢ ለውጦችን እንዴት ማሳወቅ አለብኝ?

በ Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] ውስጥ ተመዝግበው ሳሉ ገቢዎ ከተለወጠ ያንን ለውጥ በ DC Health Link [ዲሲ ሄልዝ ሊንክ] በኩል ማሳወቅ አለብዎት።

ገቢዎ ጨምሮ ለ Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] ብቁ ካልሆኑ፣ ሁኔታውን የሚያብራራ እና የ DC Health Care Exchange [ዲሲ ሄልዝ ኬር ኤክስቼንጅ] ለሚያቀርበው የጤና ሽፋን የገንዘብ እርዳታ ያገኙ እንደሆነ የሚገልጹ ሌሎች የጤና መድህን አማራጮችን የሚያቀርብ ደብዳቤ ይደርስዎታል።

# በ Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] አልተመዘገብኩም ወይም አገልግሎቶቼ ተቋርጠዋል

ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለዎት። ይግባኞች በ D.C. Office of Administrative Hearings (OAH) (ዲ.ሲ. ኦፊስ ኦፍ አድሚኒስትሬቲቭ ሂሪንግስ) ይገባሉ። የ Healthy DC (ሄልዚ ዲ.ሲ.) ሽፋንዎ እንደተከለከለ፣ እንደተቋረጠ ወይም እንደተቀነሰ የሚገልጽ ማስታወቂያ በደረሰዎት በ90 ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማለት አለብዎት። ይግባኝ ለመጠየቅ ሶስት ቅድመ ተከተሎችን መጠቀም አለብዎ።

1. የይግባኝ ቅጹን በመስመር ላይ (ኦንላይን) ከዚህ ያግኙ፦ https://oah.dc.gov/publication/request-hearing-public-benefits-case
2. የይግባኝ መጠየቂያ ቅጹን ይሙሉ
3. ከሚከተሉት መነገዶች ውስጥ አንዱን በመጠቀም ቅጹን ይሙሉ (ማመልከቻዎን በሚያስገቡበት ሰዓት ለራስዎ የቅጹን ቅጂ ሁልጊዜ ያስቀሩ)፦
   ሀ. በዚህ ኢሜይል ይላኩ፦ **oah.filing.@ dc.gov**
   ለ. ለOffice of Administrative Hearings ቢሮ በአድራሻ 441 Fourth St. NW, Suite 450N ላይ ይዘው ቢሮ ይምጡ።
   ሐ. ከላይ የተጠቀሰው አድራሻ ላይ ለOffice of Administrative Hearings በደብዳቤ ይላኩት (ይህ አማራጭ አይመከርም)

# ያለኝ የሕክምና ዕቅድ የሚያስፈልገኝን አገልግሎት ወይም ዶክተር ባይሸፍንስ?

አንዴ Healthy DC [ሄልዚ ዲሲ] ካገኙ በኋላ መብቶች አሉዎት። አገልግሎት ማግኘት ካልቻሉ ወይም ዶክተር ማየት ካልቻሉ ከእርስዎ Managed Care Organization (MCO) [ማኔጅድ ኬር ኦርጋናይዜሽን (ኤምሲኦ)] ጋር ቅሬታ (Grievance) ያቅርቡ። ቅሬታ (Grievance) ማለት ከእርስዎ MCO [ኤምሲኦ] ጋር ስላለው ችግር አቤቱታ የሚያቀርቡበት ኦፊሴላዊ መንገድ ነው። ቅሬታው ውድቅ ከተደረገ፣ በ Office of Administrative Hearings [ኦፊስ ኦፍ አድሚኒስትሬቲቭ ሂየሪንግስ] በኩል በ "Fair Hearing" (ፍትሃዊ ችሎት) ይግባኝ ማለት ይችላሉ (ከላይ ያለውን መረጃ ይመልከቱ)።